# በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መጋቢትም እንደ የካቲት

ኢዛና ዘመንፈስ

03/26/14

አንዳንድ ስለኢትዮጵያ እና ስለስለኢትዮጵያዊነት የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ግር የሚያሰኙና አሻሚ ሃሳብ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለምሳሌ "ኢትዮጵያ ማለት ከዓለም ብቸኛዋ የራሷ የዘመን አቆጣጠርና የሆነ የጽሁፍ ፊደል ወዘተ ያላት ሀገር ናት" የሚለው አስተያየት የተአማኒነት ጥያቄ እንደሚያስነሳ የሚናገሩ ወገኖች መኖራቸውን አውቃለሁ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ እንዲያው 'ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ' ሆኖ ነው እንጂ በዓላማችን እንደኢትዮጵያ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠርና ፊደል ያላቸው ሌሎች ሀገራትም አሉ" የሚል ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተም እንዲሁ እንድ ወጥ አረዳድ አለመኖሩን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ "ኢትዮጵያዊነት ማለት ከሰማኒያ በላይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ አንድ ማህበረሰብ የሚገለፁበት የጋራ እሴት ነው፡፡ ይህ የብዝሃነታችን ድምር ውጤት በጤናማ ሀገራዊ መስተጋብር እየተሰናሰለ ህብረ ብሔራዊ ገጽታ እንዲላበስ ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምሉእ ሆነው የሚገለፁት" የሚል አቋም ያላቸው አሉ። የዛኑ ያህል ይህን እሳቤ የሚቃወሙም አሉ፡፡

እንደነዚህ ሰዎች እምነት፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከብሔረሰብ ተዋጽኦ አኳያ መመዘን ለሀገር አንድነት አየበጅም። በመሆኑም "አስፈላጊና ተገቢ አይደለም" ባዮች ናቸው፡፡ ለዚህ አቋማቸው መከራከሪያ አድርገው የሚያቀርቡት "እያንዳንዱ ዜጋ እኩል ሊከበርበትና ሊኮራበት የሚችል ኢትዮጵያዊነት እያለ ጠባብ ብሔርተኝነት ላይ መንጠልጠልን ምን አመጣው?" የሚል ሃሳብ ነው፡፡ የም ሆነ ይህ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በብዙዎች ዘንድ በተደጋጋሚ የሚንፀባረቀው አለመካከት እንደየወጣንበት ህብረተሰብ ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታ ይለያያል።

ለፅሁፌ መንደርደሪያ ይሆነኝ ዘንድ ይህን ያህል ብዬ ወደ ዋነኛ ርእሰ ጉዳዬ ልተላለፍ። ከላይ የጠቀስኳቸው አንዳንድ አሻሚ አስተያየቶች የሚፈጥሩት ግርታ እንዳለ ሆኖ እኛ

ኢትዮጵያውያን፣ እንደ ህብረተሰብ የምንስማማባቸውን ሀገራዊ እውነታዎቻችንን መሰረት አድርገን የህዳሴን ዘመን ጉዞ ተያይዘነዋል።

ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደአንድ ህብረተሰብ በሌላው ዓለም ዘንድ ተለይተው የሚታወቁባቸው የጋራ የማንነት መለገጫዎች የሆኑ ሀገራዊ እሴቶች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያዊነት ከተመሠረተበትና የኢትዮጵያዊያነ ብቻ መገለጫ ከሆኑት ሀገራዊ ገጽታዎች መካከል የዘመን መቁጠር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

እናም እኛ ኢትዮጵያዊያን ባለፈው የአብሮነት ታሪካችን ኢትዮጵያውያን የብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች የጋራ ህልውናቸው መሰረት የተጣለባትን ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪም ሆነው ከውስጥ ቦርቧሪ ለመጠበቅና ነፃነaን ላለማስነካት ሲሉ የተጋፈጧቸው ፈርጀ ብዙ ፈተናዎች የጠየቁትን ዋጋ (መስዋእትነት) እየከፈሉ ያቆዩልንን ታሪክ የከወኑት በዚሁ የራሳችን በሆነው የዘመን አቆጣጠር ሥርአት ላይ ተመስርተው ነው። ይህ ማለት ደግሞ ከመላው ዓለም የኛን ሀገር ልዩ የሚያደርጋት በአንድ ዓመት ውስጥ አስራ ሶስት ወራትን በሚስተናገድ ቀመር መሰረት ከመስከረም እስከ ጳጉሜ በሚዘልቅ የጊዜ ኡደት ውስጥ እየኖሩ የየራሳቸውን ታሪክ ሰርተው ያለፉ ኢትዮጵያውያን ትውልዶች ትተውልን የሄዱትን የማይገሰስ ሀገራዊ ነፃነት ከዚህ አኳያ እያሰላን እንመረምረው ዘንድ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ለዚህ ፅሁፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መጋቢትም እንደየካቲት የሚለውን ርእስ የመረጥኩለት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቁንስ መላው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእስካዛሬው የጋራ ታሪካቸው የማይገሰስ ነፃነታቸውን አስከብረው ለመኖር ይችሉ ዘንድ ሲያካሂዱት በቆዩት የዘመናት ተጋድሎና ተጋድሎው የጠየቃቸውን ድርብርብ መስዋእትነት ሁሉ ከፍለው ያስመዘገቧቸውን ወርቃማ የድል አድራጊነት ታሪኮች ከመስከረም እስከ ጳጉሜ ባሉት 13 የኢትዮጵያውያን ወራት ውስጥ የከወኗቸው እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩን ከዚህ አኳያ አንስተን ብንመለከተው መልካም ሆኖ ስለታየኝ ነው፡፡

ይህን ሀገርኛ ርእሰ ጉዳይ ለመቃኘት ሲሞከር በተለይም ወርሃ የካቲት በኢትዮጵያ ውስጥ ካጋጠሙ ታሪካዊ ሁነቶች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ይዞ የመገኘቱ ይታወቃል። ምክንያቱም ለአፍሪካውያን ብቻም ሳይሆን ለመላው የዓለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ተደርጐ የሚቆጠረውን ታላቁን የዓድዋ ድል ጨምሮ ሌሎችም በታሪካችን

ውስጥ ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው የተጋድሏችን መገለጫዎች የተከወኑት የካቲት ወር ላይ ነው፡፡

በግልጽ አነጋገር ወርሃ የካቲት ለኢትዮጵያውያን ህዝቦች የታሪካችን ማህደር ስለመሆኑ የሚያመለክቱ እጅግ በርካታ ሀገራዊ የድል አድራጊነትና የሽንፈት ታሪካዊ አጋጣሚዎች እንዳስተናገደ ከጥንት እስከ ዛሬ የተፃፉ ልዩ ልዩ ድርሳናትን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ላነሳሁት ወቅታዊ ጉዳይ ማነፃፀሪያነት የሚያስፈልገኝን ወስጄ ሌሎቹን ለጊዜው ላቆያቸው፡፡

ከአንድ መቶ አስራ ስምንት ዓመት በፊት ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን አያቶቻችን ዓድዋ ላይ የተቀዳጁት አንፀባራቂ ድልና አሁን ሀገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የሚመሳሰሉበት በርካታ ታሪካዊ ገጽታዎች ያሉት ሆኖ ይሰማኛል፡፡ ሁለቱን ታሪኮች በእጅጉ የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች ደግሞ መሰረታዊ ሊባል የሚችል ይዘት ያላቸውና ቀላል ግምት የማይሰጠው ዓይነት ሆኖ ነው የሚሰማኝ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤

አንደኛ የዓድዋው ድል ገድልም ሆነ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዚች አገር ህዝቦች የጋራ ጥረት የተሰሩና በግዝፈታቸው ግን ለመላው አፍሪካውያን ጭምር የሚተርፍ ተምሳሌት መሆናቸው ዋናው የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ነው። የዓድዋው ድል ድምር ውጤት ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን መላውን ጥቁር ህዝብ ለፀረ ቅኝ አገዛዝ እንዲነሳሳ ያደረገና የዓለምን ታሪክ ትርጉም ባለው መልኩ የተለየ ገፅታ የሰጠ የነፃነት ጐሕ የቀደደ ክስተት እንደነበረ ሁሉ፣ አሁን ሀገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው ግድብም እንዲሁ በተለይም ለአፍሪካውያን ህዝቦች ከድህነት የሚያወጣ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፋች ነው።

ሌላው ሁለቱን ሁነቶች የሚያመሳስላቸው ገፅታ በኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መካከል የፈጠረው ሃገራዊ መግባባትና የአንድነት መንፈስ ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በዓለም አቀፍ መድረክ ተገቢ ክብር እንዲሰጣቸው በማድረግ ረገድም እንዲሁ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብን ከዓድዋው የፀረ ቅኝ ግዛት አንፀባራቂ ድል የማይተናነስ ገንቢ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ከወዲሁ መረዳት ይቻላል። ታዲያ ይህ የአድዋ ድልና የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ መሃከል ያለ መመሳሰል “መጋቢትም እንደየካቲት” አያሰኝ ይሆን?

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ የተጀመረባት መጋቢት 24 ቀን ከእንግዲህ ተራ ቀን አይደለም። በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የወደፊት ታሪክ ልዩ ስፍራ የሚሰጠውና እያንዳንዱ ዜጋ በልቡ ውስጥ ፅፎ የሚያኖረው ወርቃማ ዕለት ነው። መጋቢት 24 ቀን እንደ የካቲት 23 ቀን ሁሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይበረዝና ሳይደለዝ በሚተላለፍ ወርቃማ የታሪክ ማህደር ላይ የክብር ስፍራዋን ይዛ ይኖር ዘንድ እነሆ ታሪክ ራሱ ፈቅዷል።

ስለዚህም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በዘመኑ ዓለም ፊት ከመቸውም ጊዜ በላይ ደምቀው የሚታዩበትን አንፀባራቂ የድል አድራጊነት ታሪክ ለመስራት የታደለ ትውልድ አካል በመሆናችን ሁላችንም  ልባዊ ኩራት ሊሰማን ይገባልና እንኳን ለመጋቢት 24 ቀን 3ኛ ዓመት የድል በዓል አደረሰን። ይህን የምለው ሀገራችን በዓባይ ወንዝ የውሃ ሀብቷ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት  እየገነባችው የምትገኘው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በእርግጥም እያንዳንዱን ዜጋ ሊያኮራ የሚችል ስለመሆኑ ልባዊ እምነት ስላለኝ ነው።

አሁን ያለው የሀገራችን አጠቃላይ እውነታ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ መሆናቸውን የሚያረጋግጥልን ነባራዊ ሀቅ ጎልቶ የሚስተዋልበት የመሆኑ ጉዳይ ፈፅሞ ሊስተባበል የሚችል አይደለም። እናም ይህን ብሩህ ተስፋ የተጎናፀፈ ሀገራዊ ገጽታችንን ይበልጥ የሚያደምቁ የጋራ ዕሴቶቻችንን ወደ ላቀ ደረጃ እያሸጋገርን እንቀጥል ዘንድ ዜጎች በሞላ በጎ በጎውን ማሰብ ይጠበቅብናል። አለበለዚያ ግን ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ክብር የምንቆረቆር መስለን መታየት ብቻውን የዚችን ሀገር ህዝቦች ከድህነት ጨለማ አያወጣቸውም።

ለማንኛውም  "ታላቁን የህዳሴ ግድብ  እንደጀመርነው  እንጨርሰዋለን!!" ስንል እንደ ህብረተሰብ በታሪክ ፊት ቆመን የፈፀምነውን ሀገራዊ ቃል ኪዳን ለአንድ አፍታ እንኳን መዘንጋት ከህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት የሚጠበቅ  እንዳልሆነ ይሰማኛል። ከዚህ አኳያ የተግባር ሰው ሆነን እንገኝ ዘንድ ለየራሳችን ህሊና መታመን ይኖርብናል።

ይህ ወቅት የምንወዳት ኢተዮጵያ ከፈርጀ ብዙ ድህነት ጋር የሞት ሽረት ትግል የገጠመችበት እንደመሆኑ እያንዳንዳችን አንድ ዜጋ የሚጠበቅብህን ሁሉ ከማድረግ መቦዘን የለብንም። የተግባር ሰው ሆኖ መገኘትን ግድ የሚል ጊዜ ላይ እየኖሩ ወለም

ዘለም ማለት ትርፉ ለታሪካዊ ትዝብት መዳረግ ብቻ ነው። ስለዚህ ለገዛ ራሳችን ቃል መታመንና የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት በሚጠይቀው ትጋት ለሀገርና ወገን ዘላቂ ዕጣ ፈንታ ትርጉም ያለው ጥቅም የሚሰጥ መልካም ስራ ከውነን እንለፍ።